## መመሪያ ቁጥር 563/2013

# የፍልሰት ብሔራዊ የትብብር ጥምረት አባላትንና የሥራ ቡድኖችን አደረጃጀት እና አሰራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ

የፍልሰት አስተዳደርን ለማሳለጥና ውጤታማ ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን በብሔራዊ የትብብር ጥምረት ውስጥ በአባልነት ማካተት እንዲሁም የሥራ ቡድኖች ማደራጀት በማስፈለጉ፤

የብሂራዊ ትብብር ጥምረቱን የስራ ቡድኖች አባላትና አሰራር እንዲሁም ተግባርና ሀላፊነት በዝርዝር መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሥራ ቡድኖችና አባል ተቋማትን የግል እና የጋራ ኃላፊነታቸውን በመወሰን ተጠያቂነት ባለውና ተጨባጭ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ እንዲሰሩ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የሥራ ቡድኖችና አባል ተቋማት በቅንጅትና በትብብር ሥራዎችን እንዲያከናውኑ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

መረጃና ጥናትን መሰረት ያደረገ የክትትልና የግምገማ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

ብሔራዊ ምክር ቤቱ በሰዎች የመነገድ እና ሰውን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 35 (4) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

    ይህ መመሪያ የፍልሰት ብሔራዊ የትብብር ጥምረት አባላትንና የሥራ ቡድኖችን አደረጃጀት እና አሰራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 563/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

(1) “አዋጅ” ማለት በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ነው፤

(2) “ብሔራዊ የትብብር ጥምረት” ማለት በአዋጁ አንቀጽ 35 (1) መሰረት የተቋቋመው በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በህገ ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ መላክ ወንጀል መከላከልና መቆጣጠር ብሔራዊ የትብብር ጥምረት ነው፣

(3) “ፍልሰት” ማለት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረግ የሰው ወይም የሰዎች እንቅስቃሴ ሲሆን ስደተኞችን፣የተፈናቀሉ ሰዎችን፣ የኢኮኖሚ ፍልሰተኞችን እና ሌሎችን ያጠቃልላል፡፡

(4) በአዋጁ አንቀጽ 2 እና በፍልሰት ጉዳዮች ላይ በወጡ ሌሎች አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎች የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደየአግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

(1) በብሔራዊ የትብብር ጥምረትና አባላት፤

(2) በስራ ቡድኖችና ንዑስ የስራ ቡድኖች እና

(3) ሌሎች በፍልሰት ጉዳዮች ላይ በህግ ተግባር እና ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት እና አደረጃጀቶች፤

ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል 2</u>

## <u>ስለብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ አባላት፣ የስራ ቡድኖች አደረጃጀትና አሰራር</u>

### <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

### <u>ስለብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ አባላትና የስራ ቡድኖች አደረጃጀት</u>

4. <u>ስለ ብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ አባላት</u>

1) ብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ በአዋጁ አንቀጽ 33(3) ሥር የተዘረዘሩት አባላቱ እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን በአባልነት ያካትታል፡-

1. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር፣
2. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ግብርና ሚኒስቴር
3. የፕላንና ልማት ኮሚሽን፣
4. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣
5. የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ባለስልጣን፣
6. የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን፣
7. የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች አጀንሲ፣
8. የፌዴራል ከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፣
9. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ፣
10. የብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣
11. የተባበሩት መንግስታት የአደንዛዥ ዕጽ እና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ፣
12. የዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት፣
13. የዓለም የሥራ ድርጅት፣
14. የተባበሩ መንግስታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽን፣
15. የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መርጃ ድርጅት፣
16. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር፣
17. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካይ፣
18. የኢትዮጵያ የሐይማኖት ተቋማት ጉባኤ፣

2) ሌሎች በብሄራዊ ም/ቤቱ ሰብሳቢ እንዲካተቱ የሚደረጉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን የሚያካትት ይሆናል፣

3) የጥምረቱ አባል ተቋማት በአዋጁና በብሄራዊ ምክር ቤቱ በሚወጡ መመሪያዎች መሰረት ተግባርና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችላቸውን አሰራር ይዘረጋሉ፡፡

4) የጥምረቱ አባል ተቋማት በየተቋሞቻቸው አግባብነት ያላቸው ምክትል ሃላፊዎችን በአባልነት ይመድባሉ፡፡

## 5. <u>ስለብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ የስራ ቡድኖች</u>

(1) በብሄራዊ የትብብር ጥምረቱ ሥር የሚከተሉት የስራ ቡድኖች ተደራጅተዋል፡-

1. የግንዛቤ ፈጠራና የባህሪይ ለውጥ እና የውጭ ሐገር ሥራ ሥምሪትና ልማት  የስራ ቡድን
2. የወንጀል መከላከል እና የህግ ማስከበር የስራ ቡድን
3. የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን
4. የዳያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የስራ ቡድን
5. የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን
6. የጥናትና ምርምር የስራ ቡድን፣

(2) የስራ ቡድኖቹ እንደየነባራዊ ሁኔታው እየታዩ በየወቅቱ በብሔራዊ ምክር ቤቱ ውሳኔ ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡

## 6. <u>የግንዛቤ ፈጠራና የባህሪ ለውጥ እና የውጭ ሀገር ስራ ስምሪትና ልማት የስራ ቡድን አባላት</u>

የግንዛቤ ፈጠራና የባህሪ ለውጥ እና የውጭ ሀገር ስራ ስምሪትና ልማት የስራ ቡድን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

1) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር (ሰብሳቢ)

2) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር

3) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

4) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር

5) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

6) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

7) የስራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን

8) የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ

9) የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ

10)የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት አጀንሲ

11)የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

12)የኢትዮጵያ ሴቶች ፌዴሬሽን

13)የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን

14)የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

15)የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን

16)የኢትዮጵያ አሰሪዎች ፌዴሬሽን

17) የፋና ብሮድካስት ኮርፖሬሽን

18)የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን

19) የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ

20)ዋልታ ሚዲያ እና ኢንፎርሜሽን ማዕከል

21)የጀርመን የልማት ተራድኦ ድርጅት

22)የኢትዮጵያ ሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ

23)የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር

24)የክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ማህበር

25)የዓለም የሥራ ድርጅት

26)የዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት

27)የተባበሩት መንግስታት የአደንዛዥ ዕጽ እና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ፣

28)የውጭ ሀገር ስራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፌዴሬሽን እና

29) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት

7. <u>የወንጀል መከላከልና የህግ ማስከበር የሥራ ቡድን አባላት</u>

የወንጀል መከላከልና የህግ ማስከበር የሥራ ቡድን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

(1) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ( ሰብሳቢ)

(2) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሠላም ሚኒስቴር

(3) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

(4) የጉምሩክ ኮሚሽን

(5) የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል

(6) የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ

(7) የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት

(8) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

(9) የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

(10) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ሚኒስቴር

(11) የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች አጀንሲ

(12) የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአደገኛ እጾችና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ

(13) የዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት እና

(14) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት

8. <u>የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን አባላት</u>

የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

(1) የፌዴራል ከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ( ሰብሳቢ)

(2) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ግብርና ሚኒስቴር

(3) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር

(4) የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ

(5) የኢ.ፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

(6) የኢ.ምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲና

(7) የኢ.ፌዲሪ ጤና ሚኒስቴር

(8) የኢ.ፌዲሪ ትራንስፖርት ሚኒስቴር

(9) የኢ.ትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር

(10) የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ባለስልጣን፣

(11) የኢ.ፌዲሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

(12) የፌዴራል የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ/ኢንስቲትዩት

(13) የኢ.ንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን

(14) የዓለም ዓቀፉ የፍልሰት ደርጅት

(15) የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአደገኛ እጾችና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ

(16) ICRC

(17) አጋር ኢ.ትዮጵያ

(18) የኢ.ትዮጵያ አሰሪዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን፣

(19) የኢ.ትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን

(20) የሴቶች ማረፊያና ልማት ማህበር

(21) የዓለም የሥራ ድርጅት

(22) ኦፕሪፍስ

(23) ጉድ ሳማሪታንና

(24) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት

9. <u>የዲያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የሥራ ቡድን አባላት</u>

የዲያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የሥራ ቡድን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

(1) የኢ.ትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ( ሰብሳቢ)

(2) የኢ.ፌዲሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

(3) የኢ.ትየጵያ ኢ.ንቨስትመንት ኮሚሽን

(4) የኢ.ፌዲሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

(5) የኢ.ፌዲሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

(6) የኢ.ትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበር

(7) የኢ.ፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

(8) የኢ.ፌዲሪ ጠቅላይ ዐ/ህግ

(9) የኢ.ትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ

(10) የአለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት

(11) የአለም ስራ ድርጅት እና

(12) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት

10.<u>የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን አባላት</u>

የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

(1) ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ( ሰብሳቢ)

(2) የኢ.ፌዲሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

(3) የኢ.ፌዲሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

(4) የኢ.ፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

(5) የኢ.ፌዲሪ ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር

(6) የኢ.ምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች አጀንሲ

(7) የኢ.ትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ

(8) ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

(9) የብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን

(10) የኢ.ፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

(11) የፌዴራል ከተሞች ስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

(12) የስደተኞችና ከፍልሰት ተመላሾች ጉዳይ አጀንሲ

(13) የዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት

(14) የፕላንና ልማት ኮሚሽን

(15) የኢ.ትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና

(16) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት

11.<u>የጥናትና ምርምር የስራ ቡድን አባላት</u>

የጥናትና ምርምር የስራ ቡድን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

(1) የኢ.ፌዲሪ ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር(ሰብሳቢ)

(2) የኢ.ፌዲሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

(3) የኢ.ፌዲሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

(4) የኢ.ምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች አጀንሲ

(5) ህግና ፍትህ ስልጠና ምርምር ተቋም

(6) የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲቱት

(7) የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

(8) አለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት

(9) የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአደገኛ እጾችና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ

(10) ብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን

(11) የአለም የስራ ድርጅት

(12) የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እና

(13) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት

**<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>ስለ ሥራ ቡድኖች ዝርዝር አሰራር</u>**

12.**<u>ጠቅላላ</u>**

(1) እያንዳንዱ የሥራ ቡድን እንደአስፈላጊነቱ በሥሩ ንዑስ ቡድኖችን ሊያደራጅ ይችላል፡፡

(2) በስራ ቡድኖች ዉስጥ የሚሳተፉ ተቋማት ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ተወካይ ይመድባሉ፤ ተወካዮችም የስራ ክፍሉ ሀላፊ ወይም ምክትል ሃላፊ ይሆናሉ፡፡

(3) የሥራ ቡድኖች ከብሄራዊ የትብብር ጥምረቱና ከሌሎች የጥምረቱ የስራ ቡድኖች እቅዶች ጋር የሚጣጣም የራሳቸው እቅድ ይኖራቸዋል፡፡ የሚወጣው እቅድም የየተቋማቱን የስራ ድርሻ በግልፅ መለየት የሚኖርበት ሲሆን በጋራ ሊሰሩ የሚገባ ስራዎች ካሉ ይኸው ተለይቶ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

(4) የስራ ቡድኖች የሴቶች፣ የህጻናት፣ የአዕምሮ ህመምተኞች እና የአካል ጉዳተኞችን ለአደጋ ተጋላጭነትና ልዩ ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ተግባርና ሀላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

(5) የስራ ቡድኖች የሚያዘጋጇቸው ዕቅዶችና ሪፖርቶች በአጠቃላይ የሚይዟቸው መረጃዎች በጾታና በእድሜ የተከፋፈለ ሊሆን ይገባል፡፡

(6) ሁሉም የስራ ቡድኖች ስራቸውን በተቀናጀና በተናበበ መልኩ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ የስራ ቡድኖች ወይም ተቋማት በሌላ ቡድን የተካተተ ተቋም ድጋፍ በሚያስፈልግ ጊዜ እነዚሁ ተቋማት አስፈላጊዉን ድጋፍ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል፡፡

(7) የሥራ ቡድኑ ተሳታፊ ተቋማትም የተሰጣቸውን የስራ ድርሻ በመውሰድ በተቋማቸው ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ የተሰሩ ስራዎችንም ለቡድን ሰብሳቢ ተቋማት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡

(8) የእያንዳንዱ የስራ ቡድን ሰብሳቢ ለጥምረቱ ሰብሳቢ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## 13. <u>የግንዛቤ ፈጠራና የባህሪይ ለውጥ እና የውጭ ሐገር ሥራ ሥምሪት የስራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) ስለፍልሰት ምንነት፣ ስላሉት አወንታዊና አሉታዊ ጎኖች እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ይሰራል፤

2) ዜጎች በሃገራቸው ሰርተው መለወጥ እንደሚችሉ የማስገንዘብ ሥራ ይሰራል፤በአካባቢያቸው ስላሉ እድሎች የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ይሰራል፤

3) ውጭ ሀገር ሄደው መስራት ለሚፈልጉ ዜጎች ስላሉ ህጋዊ አማራጮች ግንዛቤ ይፈጥራል፤

4) ለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች የስራ እድል እንዲፈጠር ከፍልሰት ተመላሾችና የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድንና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

5) የሀይማኖት አባቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ታዋቂ ግለሰቦችን እና ሌሎችን ባሳተፈ መልኩ ማህበረሰቡ የችግሩን መንስኤ እንዲያውቅና እንዲለይ፣ የመፍትሄውም አካል እንዲሆን በማድረግ አሳታፊነት ያላቸው የመማማሪያና የባህሪ ለውጥ መፍጠሪያ የማህበረሰብ ወይይቶች እንዲመቻቹ ያደርጋል፤ ይደግፋል፤

6) ከፍልሰት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ የኪነጥበብ ውጤቶችን በመጠቀም ለማህበረሰቡ ትምህረት እንዲሰጥ ያደርጋል፤ የችግሩን አስከፊነት የሚያብራሩ የተለያዩ በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት ለተደራሾች ያሰራጫል፤ የአደደባባይ ማስታዎቂያዎችን (ቢልቦርዶችን) በመትከልና ሌሎች መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም አስተማሪ መልዕክቶችን ያስተላልፋል፤

7) የመንግስትና የግል መገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ስለ ፍልሰት ጉዳዮች ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን፣ ዘገባዎችንና ሌሎች ስራዎችን ለህዝብ ተደራሽ ያደርጋል፤

8) ዜጎች ስለ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ፍልሰት በተለይም ከፍልሰት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በመጸየፍ በመልካም ሥነምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ለማስቻል ጉዳዩ በትምህረት ካሊክለም እንዲካተት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመሳተፍ  የማማሪያ መድረክ እንዲፈጠርላቸው ክትትል ያደርጋል፤

9) አስተማሪ የሆኑ የሀገራችን እና የሌሎች ሀገራት ዜጎችን የፍልሰት ተሞክሮ በመቀመር የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ይሰራል፤

10)እንደአስፈላጊነቱ ከጥናት ከትትልና ግምገማ የስራ ቡድን ጋር በመቀናጀት አስተማሪ ጽሁፎችን ያዘጋጃል፤ በተሰሩ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች  ስለአስገኙት የባህርይ ለውጥ ዳሰሳዊ ጥናት ያደርጋል፡፡ ችግሮችን በመለየት ተግባራዊ ምላሽ ይሰጣል፡፡ እንዲሰጥም ያደርጋል፣

11)አዋጅ ቁጥር 923/2008 በትክክል ስራ ላይ እንዲውል ይሰራል፤

12)ከሥራ ስምሪት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከተቀባይ አገራት ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት ሊደረግ ስለሚችልበት ሁኔታ እንዲጠናና አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ከጥምረቱ ጋር በቅርበት ይሰራል፤ ዜጎቻችን ሊቀጠሩባቸው የሚችሉባቸውን የስራ መስኮች ይለያል፤

13)በውጭ ሀገር ለስራ የተሰማሩ ዜጎች ሰብዓዊ መብቶቻቸው እና ደህንነታቸው የተከበሩላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

14)በተቀባይ አገር ውስጥ በዜጎች ላይ የመብት መጣስ ወይም ጉዳት ሲደርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለዚሁ ተጠያቂ በሆኑ ሰዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይሰራል፤

15)ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ ተጎጂ ለሆኑ ዜጎች ከተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን እንዲሁም ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ ድጋፎች እንዲያገኙ ይሰራል፤

16)ከውጭ ሀገር የስራ ስምሪት ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ከወንጀል መከላከልና ህግ ማስከበር የስራ ቡድን ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

17)የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራል፣ያስተባብራል እንዲሁም፣

18)ሌሎች መሰል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 14.<u>የወንጀል መከላከል እና የህግ ማስከበር የስራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) ህብረተሰቡ በፍልሰት ጉዳይ የወጡ ህጎችን እንዲገነዘብ ያደርጋል፤ ተጎጅዎች ያላቸውን ልዩ መብት እንዲያውቁ ያደርጋል፤
2) በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር ሲያቋርጡ የተገኙ ዜጎችን በመመለስ በጊዜያዊ የመጠለያ ማዕከላት እንዲቆዩ ያደርጋል፤እነዚህንም ለተጎጅዎችና የችግሩ ሰለባዎች ድጋፍ ቡድን በማሳዎቅ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

3) የተጎጂዎችን መብት ማዕከል ያደረገ የተጠናከረና የተቀናጀ የድንበር ቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

4) የወንጀል መከላከል እና የህግ ማስከበር ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተሻለ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲኖር ይሰራል፤

5) በፍልሰት ጉዳይ የወጡ ህጎችን አተገባበር ከጥናትና ምርምር የስራ ቡድን ጋር በመተባበር በማጥናት ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው አካላት ሀሳብ ያቀርባል፤

6) የህግ ማስከበር ስራውን ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ያዘምናል፤

7) የወንጀል መከላከልና የህግ ማስከበር አሰራሮችን ለማሻሻል የሚያስችሉ የህግ አስከባሪ ባለሙያዎችን አቅም የማጎልበት ስራ ይሰራል፤

8) የግለሰቦች የግል ሕይዎት የመጠበቅና የመከበር መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ሰለባዎችን ታሪክ የወንጀል ምርመራና ፍርድ ሂደቶችን በተለያዩ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለማህበረሰቡ እንዲደርሱ እና እንዲማርባቸው ያደርጋል፣ እንዲሁም

9) ሌሎች መሰል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

15.<u>የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት</u>

(1) ተጎጅዎችን በኢኮኖሚ፣ በጤና፣ በስነ-ልቦናና በማህበራዊ ህይወት ጉዳዮች የመደገፍና የማቋቋም ስራ ይሰራል፤

(2) ድገፍ ሊያገኙ የሚገባቸውን ተጎጅዎች የመለየት ስራ ይሰራል፤ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ድጋፍ የሚሹ ተጎጅዎችን መለያ መለኪያ (Victims Referral Standards) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያወጣል፤

(3) ተጎጂዎችን በሚመለከት በሚወጡ ህጎች አተገባበር ላይ ክፍተቶችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንደወሰድ ለሚመለከተው አካል ሀሳብ ያቀርባል፤

(4) በአገልግሎት ሰጪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መካከል የተቀናጀ የተጎጂዎች አገልግሎት አሰጣጥና ቅብብብሎሽ እንዲኖር ያስተባብራል፤

(5) ተጎጂዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት የግል ዘርፉን ያሳትፋል፣ ያስተባብራል፤

(6) ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፣ ያስተባብራል፤

(7) ተጎጂዎችን ለመደገፍና ለማቋቋም ከሌሎች የብሔራዊ ጥምረቱ የሥራ ቡድኖችና አጋር አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል እንዲሁም

(8) ሌሎች መሰል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

16.<u>የዳያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የሥራ ቡድን ተግባርና ሃላፊነት</u>

1) የዳያስፖራ አባላትን በሀገራቸው የልማት ጉዳይ በተለይም የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ከማሳደግ፤ በኢንቨስትመንት መስክ እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ በያገባኛል ስሜት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታዎች መዘርጋታቸውን ይከታተላል፤

2) ከዳያስፖራው የሚገኙ የእውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እድሎችን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፤

3) የግብረሰናይና የልማት ማህበራትን በኢትዮጵያ የልማትና ሌሎች ጉዳዮች ላይ እንዲያግዙ ያተጋል፤

4) የዳያስፖራው ማህበረሰብ ባህላቸውንና ታሪካቸውን የሚያውቁበትና የሚያዳብሩበት ምቹ ሁኔታወች እንዲፈጠሩ ይሰራል፣ያስተባብራል፤

5) የዳያስፖራው ማህበረሰብ ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታዎችን እንዲከታተሉ በማንቃት/በማድረግ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና ገጽታ እንዲያስጠብቁ ይሰራል፤

6) በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዜጎቻችን መብት፣ ክብር፣ ጥቅምና ደህንነት ያስጠብቃል፤ የህግ አገልግሎት ይሰጣል እንዲሁም

7) ሌሎች መሰል ተግባራትን ይሰራል፡፡

17.<u>የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን ተግባርና ሀላፊነት</u>

1) ከፍልሰት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካላት በመሰብሰብ የተሟላና ወጥ የሆነ ሀገራዊ የፍልሰት መረጃ ቋት ያደራጃል፣ይተነትናል፣ ያስተዳድራል፤ እንደአስፈላጊነቱ ለህዝብ ተደራሽ ያደርጋል፤

2) አግባብነት ባላቸው አካላት ሲጠየቅም መረጃ ይሰጣል፤

3) የተቀናጀ የፍልሰት መረጃ ልውውጥ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል እንዲሁም

4) ሌሎች መሰል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

18.<u>የጥናትና ምርምር የስራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የተቀናጀ የፍልሰት አስተዳደር ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት ከስራ ቡድኖች እና ከብሄራዊ የትብብር ጥምረቱ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር እንዲካሄድ ያደርጋል፤

2) ከዚህ ቀደም በፍልሰት ዙሪያ የተጠኑና በየወቅቱ የሚከናወኑ ጥናቶችን በማሰባሰብ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

3) የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በፍልሰት ዙሪያ ጥናት እንዲካሄዱ የማስተባበር ስራ ይሰራል፤

4) ሌሎች መሰል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

19.<u>የሰብሳቢ ተቋማት ተግባርና ሀላፊነት</u>

1) የስራ ቡድኑን አባል ተቋማትን ያስተባብራል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤በአግባቡ ተግባርና ሀላፊነታቸውን የማይወጡ ተቋትን በተመለከተ ተገቢውን የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

2) የቡድኑን የስራ እንቅስቃሴ መረጃዎች ያደራጃል፤

3) የጋራ እቅድና ሪፖርት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ለጥምረቱ ጽ/ቤት የተጠቃለለ ሪፖርት ያደርጋል

4) ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ይፈጽማል፡፡

20.<u>ስለ ጥምረቱና የስራ ቡድኖቹ መደበኛ ሥብሰባ</u>

(1) ጥምረቱ በየሩብ አመቱ ይሰበሰባል፤

(2) እያንዳንዱ የሥራ ቡድን በየሁለት ወሩ ይሰበሰባል፤

(3) ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጊዜውን ያልጠበቀ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

<u>**ክፍል ሶስት**</u>

<u>**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**</u>

21.<u>**የመተባበር ግዴታ**</u>

ማንኛውም አካል ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

22.<u>**መመሪያውን ስለማሻሻል**</u>

የፍልሰት ብሔራዊ ምክር ቤቱ ይህ መመሪያ ሊሻሻል ይገባዋል ብሎ ሲያምን የማሻሻል ስልጣን አለው፡፡

23.<u>**መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ መመሪያ ከ---ወር--ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡